# <u>ለምን ይዋሻል? እስከመቼስ ይዋሻል?</u>

**ቁጥር 9**

ውሸት ደግ ነበር ጣጣው ባልነበር እንደተባለው ሁሉ በቃል ተነግሮ ከሚተነው ውሸት በላይ
መዘዘኛው ደግሞ በወረቀት ላይ የሚሰፍረው ነው፡፡ ሞኝና ወረቀት ያስያዙትን አይለቅም እንደ
ሚባለው መሆኑ ነው፡፡ የወያኔና ጭፍሮቹ ውሸት በራዲዮ ና በቴሌቪዥን፤ ማለትም በቃል በአለ
-ባልተኞችና ዋሾዎች መሰራጨት ብቻ ሳይሆን በተለይ በአሁኑ ጊዜ በመፅሀፍ መልክ በሰፊው
እየተነዛ ነው፡፡ በሀገር ቤት ያለው ዜጋ የመፅሀፍ ማንበብ ጉጉቱ እየጨመረ መምጣቱ ደስ የሚያ
ሰኝ ቢሆንም ሀቁን መሰረት አድርገው የሚታተሙ መፅሃፍት ቁጥር በጣም ጥቂት ነው፡፡ በአንፃሩ
የወያኔ ቅጥረኞችና ነበርን አወቅን ባዮች የሀሰት መርዛቸውን የሚረጩባቸው መፅሀፍት በብዛት
በወያኔ በጎ ፍቃድ ይታተማሉ፡፡ የማያውቁትን አወቅን ብለው የወያኔን ፀ-ረ ኢሕአፓ ሀሰት በማ
ሰራጨት ከወያኔ እርጥባን ፈላጊ ቅጥረኛ ባለብዕሮችም እየፈሉ ናቸው፡፡ በጥቅሉ ምላሽን
መጠየቃቸው አልቀረም፡፡

መለስ ዜናዊን ፤ ስዩም መስፍንን፤ ወያኔን እንደ ድርጅት የሚያደንቁ መፅሀፍት ብቅ ብለው
ወያኔ ራሱ በሺዎች እየገዛ በማሰራጨት ላይ ነው፡፡ በነዚህ መፅሀፍት ውስጥ ተራራን ያንቀጠቀ
ጠ ትውልድ በሚሉት ቅፆች የተጀመረው ፀረ ኢሕአፓ ውሸት ተስተጋብቶና ተስፋፍቶ ይገኛል፡፡
የሀገራችን ሰው ግን በመፀሀፍም ሊዋሽ እንደሚችል ጠንቅቆ የሚያውቀው ነው፡፡ አፄ ኃይለ
ሥላሴ ን ለምሳሌ ለማስደሰት ብዕር ያነሱ ልጅ እያሱን ማጥላላታቸው የሚጠበቅ ነው፡፡ አንድ
ጠባብ የኦሮሞ ምሁር ለምሳሌ ከፈረንጅ ጋር ሆኖ ኢትዮጵያ የለየችና ከገዋ ከአየር የተሰረፀች
ልብ ወለድ ናት ብሎ ብዙ ገፆች ያሉት መፅሀፍ ከትቧል፡፡ በመፅሀፍ መልክም ይዋሻል፡፡ የደርግ
አረመኔዎች ወይም ቀይ ሽብር አራማጆችም በበኩላቸው ምስክር ሆንን እያሉ ምን ያህል በፀረ
ኢሕአፓ ውሸት መሰማራታቸውን የታዘብነው ነው፡፡ መሰል መፅሀፍትን ወያኔ በፍቅር ያሰራጫቸ
ዋል፡፡ ሕዝብን ከሕዝብ ለማናከስ የተፃፉ ብልሹ ትረካዎችም ዛሬ በኢትዮጵያ ገበያ እየተሸጡ
ናቸው፡፡ የመፅሀፍቱንና ደራሲዎቹን ስም መጥቀሱ ክብር መስጠት ይሆናል በሚል የምናልፈው
ሲሆን ስለ ኢሕአፓ ሀቁ ሰፍሮና ተፅፎ ያለ ቢሆንም አሻፈረን ብለው መቀላመዱን የሚመርጡ
ሌሎችም መኖራቸው ደግሞ እየታተሙ ካሉ ራሳቸውን ታሪክ ተራኪ ከሚሉ መፅሀፍት ልንረዳ
ው የምንችለው ነው፡፡ ለሀቁ ከቶም ግድ የሌላቸውና አንዱ ገፅ ሌላውን የሚቃረን አድርገው
መፃፋቸው የማይታያቸው “ ፀሀፊዎች” በርክተዋል፡፡ ዋናው ቁም ነገር የተወሰኑ ገፆችን በሽፋኖ
ች መሀል ሰብስቦና ጠርዞ ማውጣት መፅሀፍ መፃፍ የሚመስላቸው በርክተዋል፡፡ በመሆኑም በኢሕ
አፓ ላይ ውሸት በውሸት ላይ እየጨማመሩ ይፅፋሉ፡፡ የወያኔዎቹ የሚጠበቅና የሚገባን ሲሆን.፤
የደርግ ወንጀለኞች ኢሕአፓን በሀሰት በመክሰስ ሊያካሂዱ የሚጥሩት የራስ መከላከል የሚታየን
ም ቢሆን ሌሎች ግን ነበርን ባዮች እየረጩት ያለው ሀሰት ግን ልዩ ውግዘትን መጠየቁ የሚያከ
ራክር አይደለም፡፡

የየካቲትን አብዮት ታሪክ ማን ሊፅፍ የሚል አጋጅ  አቅዋም ባይኖረንም ሊፅፍ የሚቃጣ ሲሆን በእንቅስቃሴው የተካፈለ አሊያም በቂ ጥናት ያደረገና ሀቀኛ መረጃ የሰበሰበ መሆን አለበት/አለባት፡፡ የኢሕአፓ አመራር አባላት በአዲስ አበባ በምስጢር ተሰብስበው በመንግስቱ ላይ የሞት ፍርድ ፈረዱ ብሎ ከዚያም የፈራጆቹን ማለትም የኢሕአፓ መሪዎችን ስም ዝርዝር ሲደረድሩ የመኢሶንም ማዕከላዊ ኮሚቴዎችን ስም ኢሕአፓ ብሎ ማቅረቡ ውይም በከተማ ያልነበሩትን መሪዎች ነበሩ ማለቱ ውሸት ከመሆን አያመልጥም፡፡ ፀሀፊው በሌላ ባይከሰስ በግብር ይውጣ መፃፉና ለሀቅ ምንም ሚዛን አለመስጠቱ የሚያስወቅሰው ይሆናል፡፡ በቀይ ሽብር ተጠያቂ መሆን የሚገባው አንድ ሻምበል ለምሳሌ ወያኔን ለማስደሰት በፃፈው መፅሀፍ ኢሕአፓን ምዕራብ ጀርመንና  የአልጄሪያ መንግሥት ተባብረው መሰረቱት ሲል ተቀዷል፡፡ እንዴት? ኢሕአፓ በተመሰረተበት ጊዜ ምዕራብ ጀርመንና አልጄሪያ ወዳጅ አለመሆናቸውን የሚያውቅ የለም ብሎ ነው? አልጄሪያ ሶሻሊስትና ተራማጅ ተብላ ከምስራቅ ጀርመን የወገነች ሀገር ከመሆኗ ሌላ ምዕራብ ጀርመን የአፄው መንግሥት ደጋፊ ምስራቅ ጀርመን ደግሞ ተቃዋሚ እንደነበሩ የሚያውቅ የለም ብሎ ነው ያሰኛል፡፡ የፀሀፊ ተብዬው ዋና ዓላማ ግን ኢሕአፓን ማጥላላት፣ መስደብ፣ በባዕዳን የተመሰረተ ፀረ ኢትዮጵያ እንቅስቃሴ ለማለት በመሆኑ ለሀቁ ቦታ የለውም፡፡

የኢሕአፓን ታሪክ ፃፍን ያሉ ግለሰቦች መኖራቸው ይታወቃል--ዛሬ በኢሕአፓ ያሉት አይደሉም ፡፡ ከድርጅቱ የወጡ ወይም ወጥተው ከደርግ ሆነ ከወያኔ ጋር ያበሩ ግን ፃፍን ብለው መፅሃፋቸውን አቅርበዋል፣ ለማቅረብም እየተዘጋጁ ናቸው፡፡ ኢሕአፓ ይህንን በተመለከተ ያለውን አቅዋም ከዓመታት በፊት ግልፅ ማደርጉ የሚታወስ ነው፡፡ በየካቲት 1986 ዓ.ም. “ታሪክ እንዳይጎድፍ” በሚል ርዕስ ከወጣው ፅሁፍ እንጥቀስ፣

*“ የኢሕአፓ ታሪክ ሰፊ ነው፡፡ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ለስር ነቀል ለውጥ ምርጫ ጆሮ ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ መነሳትን ይጠይቃል፡፡ ለድርጅቱ ምስረታ የተደረጉትን ጥረቶች በየአቅጣጫው ማወቅን፣ እስካሁን ምስጢር ሆነው ያሉ ግንኙነቶችንና ከንዋኔዎችን ወዘተ .. ጠንቅቆ ማወቀን የግድ ይላል፡፡ በኢሕአፓ አመራር ከምስረታ ጀምሮ የቆየ ግለሰብ እንኳን የድርጅቱን ታሪክ በተሟላና ሚዛናዊነቱ አጥጋቢ በሆነ መንገድ ለመፃፍ አይቻለውም፡፡ ይህ ታሪክ ሙሉ በሙሉ ይፃፍ ከተባለ የብዙ መሪዎችን፣ አባላትን ወዘተ ተሳትፎና አስተዋፅዖ ይጠይቃል፡፡”*

የኢሕአፓን ታሪክ ፃፍኩ ያለውን የመጀመሪያ ግለሰብ በተመለከተ በጊዜው ተገቢው ሂሰ መደረጉና እርምቶችም መቅረባቸው የሚታወስ ነው፡፡ ድርጅቱን ከለቀቁ ዓመታት ያስቆጠሩ ወይም በድርጅቱና በሰራዊቱ ተሳትፎአቸው ደቃቃና የጥቂት ጊዜ የሆነ ስለ ድርጅቱም ሆነ ሠራዊቱ ኢሕአሠ ለመፃፍ በቂ መሰረት አይኖራቸውም፡፡ ድክመታቸውን ለመሸፈን ደግሞ በቂና ሀቅ የሆነ መረጃ መሰብሰብ ሲገባቸው አንድም የራሳቸውን ታሪክና ድርጊት ለመከላከል አሊያም ወያኔን

ለማስደሰት ሲሉ የማይመቹ ሀቆችን አልሰማንም ባይ ሆነው ይነሳሉ:: መፅሀፍ ፀሀፊዎቹ ከኢሕአ ፐ ጋር ከተለያዩ ብዙ ዓመታት ማለፉ እየታወቀ እንዴት ስለማያውቁት ድርጅት ወይም ሠራዊ ት ሊፅፉ ይነሳሉ--በተለይም ያን ቁርሾአቸውን ወደ ጎን ትተው ሀቁን መቀበልና መቅረብ ተስኗ ቸው እያለ ? ለምሳሌ በቅርቡ ስለ ሠራዊቱም ስለድርጅቱም መፅሀፍት ላወጣ ነው ብሎ ሲለፍፍ ለተደመጠ አንድ ግለሰብ ቃለ መጠይቅ አቅራቢዎቹ በሠራዊቱ የነበረውን ሚና ሲጠይቁት ኢምንት መሆኑንና ራሱም ሠራዊቱን የተቀላቀለው ቆይቶ መሆኑን ሊደብቅ አልቻለም:: ይኸው ግለሰብ ግን ስለ ሠራዊቱ የመጀመሪያ ዓመታት ስለ ድርጅቱም እንዲሁ መለፈፍ ብቻ ሳይሆን በስማ በለው፣ አቦ ሰጡኝና አልፎም የወያኔን ውሸቶች በማደስ መፅሀፍትም ፃፍኩ እያለን ነው:: በዚህም መሰረት ያወቀ መስሎት የተደጋገመ ውሸትን አድሶ ያቀርባል:: የኢሕአፓ ሠራዊት የብተና አደጋ ከደረሰበት በኋላ ለረጅም ዓመታት በትጥቅ ትግሉ ተሰማርቶ ብዙ ውጣ ውረዶችን አልፏል:: ፃፍን ባዮቹ የማያወቁትና ያልነበሩበት ትግል ነው:: ታሪክ ብሎ የመጀመሪያውን መፅሀፍ ያቀረበው ግለሰብ አቅጣጫውን የሳተ ትግል ብሎ አውግዞት የተወውን ትግል ኢሕአፓዎ ች ለረጅም ዓመታት መቀጠላቸውና ግለሰቡ ከወያኔ ጋር እየታገሉ መገዛትን አቅዋም ይዞ ሲግባባ የቀጠለውን ፀረ ወያኔ ኢሕአፓንስ እንዴት ቦታ ሊሰጠው ወይም ሊያውቀው ይችላል? በአጭሩ የኢሕአፓን ሀቀኛ ታሪክ ሊፃፍ የሚችለው በኢሕአፓዎች እንጂ በታኞች፣አንጃዎች ወይም የወያ ኔ ተለጣፊ የሆኑ ማፈሪያዎች ሊፅፉት አይችሉም ማለት ነው:: ተረት ተረት ውሸት ውሸት ካልሆ ነ ::

ክታብ የበጠሱ ወይም ቃል ኪዳናቸውን የካዱ ( ጥምጥም የፈቱ) ሁሉ የባሰባቸው ለመሆናቸው ተመክሮ ያስተምረናል:: ብዙውን ጊዜ ከመምህሩ ደቀ መዝሙሩ የሚባልባቸው መሰል ፍጡሮች ናቸው:: ይድረስ ምናምን ብሎ የፃፈው ግለሰብ ለምሳሌ ገና ትግሉ ሲጀምር የከዳ ሆኖ ሳለ መፅሀ ፉ ውስጥ ግን ራሱን ሁሉን አራጊ ፈጣሪ አድርጎና ራሱን ክቦ መተረቱ አልቀረም:: መስመር ሲቀይሩና ለአዲስ ጌታ ሊያደሩም ሲነሱ የነበሩበትን ማውገዝና መጨፍጨፍ የተለመደና የሚጠ በቅ ነው:: ሽንፈትን ተከትሎ ወይም ትግል ሲራዘም የሚመጣ በሽታ ነው:: ከቀይም ቀይ እሳት ነን ያሉ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ማኦንም ተከታይ ነን ያሉ ሁኔታው ሲጠጥር ከአድህሪም አድህሪ ሲሆኑ አይተናል:: በግልባጩም ይሰራል:: ንጉሱ ምን አጠፉ ባዮችና የአፍቅሮ ዘውድ ምሳሌዎች ደርግ ሲመጣ ልብስ ቀይረው በሶሻሊዝም ስም ሲምሉና ሌሎችን አድሃሪ ብለው ሲያወግዙና ሲያ ዋክቡ ታዝበናል:: ኑዛዜያቸውም ሁሌ በ " እኛ ያኔ " መጀመሩ የተለመደ ነው:: በድርጅቱም ሆነ በሠራዊቱ የነበራቸው ቆይታና ሚና ከገባ ወጣ ባይለይም ያኔ እኛ ብለው የሚያወሩት ግን ገደ ብ አልባ ይሆናል:: ሀቀኛ ታሪካቸው ሲመረምርም ጓዶችን ሲያጋልጡና አሳልፈው ሲጡና ሲያሰ ቃዩ የነበሩ ግንቦቴዎች መሆናቸውም ይታያል:: ታሪክን ሊሸር ተነስቶ ታሪክ ፃፍኩ ወይ ልፅፍ ተነሳሁ የሚለን ሀፍረተ ቢስ ግለሰብ ለምሳሌ በሠራዊቱ የቆየው ለጥቂት ጊዜ ቢሆንም በሕዝቡ ላይ ርዕዮታችንን ጫንበትና ሀይማኖተኛው ሕዝብ አልተቀበልንምብሎ ለጋዜጣ መግለጫ ሰጥቷ ል:: ይህን የሀሰት መርዝ እንዲረጭ መድረክ ሰጪዎቹ የዛሬ ወዳጆቹ የወያኔ ተለጣፊዎች ሊሆኑ መቻላቸው የሚገመት ነው:: ግለሰቡ ያለው ላይ ከመተቸታችን በፊት ይኸው ሰው ስለ ሠራዊቱ

የምስረታ ሂደት፤የእርሾ ሀይል ስልጠና ቦታ፤ ወዘተ እንዲሁ የፃፈው ውሸት መሆኑን መጥቀስም ይቻላል::

ኢሕአፓ ፀረ ሀይማኖት ነኝ ብሎ በሀይማኖቶች ላይ በአሉታዊ ተነሳ? ሰበከ? እርምጃ ወሰደ? በሠራዊት ያለፈ ቀርቶ ያላለፈም ለዚህ መልሱ የሚጠፋው አይደለም:: ኢሕአፓ አቅዋሙን ከሕዝብ ጋር አጣጥሞ ሊታገል የጣረ ድርጅት ነው:: በአቅዋም ደረጃ ፀሀፊው ባይገባውም ኢሕአፓ ይታገል የነበረው ኮምዩኒዝምን ወይም ሶሻሊዝምን በዚያን ጊዜ በሀገር ለማስፈን ሳይሆን አዲስ ዴሞክራሲያዊ አብዮትን ለማካሄድ ነበር:: ይህም መሰረቱ አርሶ አደሩና ለባደሩ የሆነና ሰፊውን ሐዝብ የሚያቅፈና የሰፊውን ሕዝብ ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጥ ትግልና አብዮት ነበር:: እንዴት ታዲያ በሀይማኖት ጉዳይ ከሰፊው ሕዝብ ሊጣላ ኢሕአፓ ይወስናል? ስለዚህም ኢሕአፓ በቅስቀሳም ሆነ በፕሮግራም ደረጃ ፀረ ሀይማኖት አቅዋም መቸም ይዞ አያውቅም:: ወያኔ ካድሬ ወን ቆጳስ እንዳለው በትግራይም፤ በጎንደርም በጎጃምም ባለፈበት ደብር ሁሉ የራሱን አባል ሀላፊ ካህን እያለ አልሾመም:: በሀይማኖት መሰረት ልዩነት አይደረግ ከማለትና መንግስትና ሀይማኖት መለያየት አለባቸው (”ሴኩላሪዝም መስፈን አለበት) ከማለት ሌላ ሀይማኖትን በተመለከተ ኢሕአፓ ያደረገው አሉታዊ ቅስቀሳ አልነበረም/ዛሬም የለም:: በሠራዊቱ አንዳንድ ፀሀፊውን መሰል ጥራዝ ነጠቆች የለፈፉት ከነበረም ወዲያው የሚታረም ለመሆኑ ሁሉም የሚያወቅው ነው:: ከአቅዋም አልፎ ግን ኢሕአሠ በተንቅሳቀሰባቸው ቦታዎች ሁሉ የሁሉም ሀይማኖት አማኞችን በአግባቡ ከመያዝ አልፎ ድጋፍ የሰጠ መሆኑን ታሪክና ያልከዱት አባሎቹ ይመሰክራሉ:: ዋልድባ፤ ማህበረ ሥላሴ፤፤ ዮፍታህ ጊዮርጊስና ሌሎችም ቤተ ክርስቲያኖችንና ገዳማትን በተጨባጭ በቆሳቁሰም ረድቷል:: በጎንደርና በትግራይ የሚገኙ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮችና የይሁዳ ሃይማኖት ተከታዮች ማለትም ቤተ እስራኤሎች መብታቸው እንዲከበር አድርጓል:: ከዚህ በተጨማሪ በዝርዝር ይህን አደረገ ያን አደረገ ማለቱ ተገቢ አይሆንም:: የሠራዊቱ በርካታ አባላትም የተለያዩ ሃየማኖት ተከታዮች የነበሩ መሆናቸውም የሚታወቅ ሆኖ ሳለ ድርጅቱ አማኝ ሕዝብ ላይ ፀረ ሀይማኖት ርዕዮት ጫነበት ብሎ መለፈፍ መሰሪ ውሸት ከመሆን ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? ኢሕአፓ ፀረ ሀይማኖት ቢሆን የአማኞችን፤ የቀሳውስትን፤ የባሕታዊያን፤ የእስላሞችንም ወዘተ ድጋፍን ያገኝ ነበር? እነዚህ ዓይነቶቹ ዋሾዎች ናቸው ታዲያ ነበርን አወቅን ብለው ስለ ኢሕአፓ የባጡን የቆጡን የሚቀባጥሩት!

በአሁኑ ጊዜ የኢሕአፓ እንቅስቃሴ እየተጠናከረ በመምጣቱ የተቅበዘበዙት ወያኔዎች ብቻ አይደሉም:: እነ መጣብንም ጩንቋቸዋል:: ድርጅቱንና ሕዝብን ክደው ለወያኔ የሰገዱትም መራድ ጀምረዋል:: የኢሕአፓ ወጣት ክንፍም መንቀሳቀስ በመጀመሩ የወጣቱን ታሪክ ልንፅፍ ነው ብለው መራወጥም የጀመሩ አሉ:: ለደግ ሳይሆን ለለመደው አፍራሽና ወያኔን ጠቃሚ ተልዕኮአቸው መሆኑ መሳት የለበትም:: በመሆኑም ከመቸውም ጊዜ በበለጠ በየአቅጣጫው በኢሕአፓ ላይ ውሸት እየጎረፈ ነው:: መፅሀፍቱም መፍላታቸው የሚጠበቅ ነው:: በዚህም በዚያም ግን ከቶም ሊለወጡ የማይችሉ ሀቆች አሉ:: ወያኔም፤ የደርግ ወንጀለኞችም ሆኑ የእነ ነበርን ጫጫታ

ሊያፍነው የማይችለው ሀቅ ኢሕአፓን ይገልፀዋል:: የውሸት ጋጋታ ሀቁ ብቅ እስኪል ነውናም የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዛኛው ኢሕአፓን የሚያይበት ዓይን ሊንሸዋረርና በዚያውም ተበላሽቶ ሊቆይ የሚችልበት ምንም ምክንያት ወይም ሁኔታ የለም:: ኢሕአፓ የሕዝብን ሰፊ ድጋፍ ያገኘ ድርጅት መሆኑን የሚክዱ ጥቂቶች ናቸው:: ይህን መሰል ሰፊ ድጋፍ ማግኘት የቻለው የሕዝብን ሰቆቃ በማስተጋባቱ፤ የሕዝብን መፈክሮች በማንገቡና ለሕዝብ ጥቅም በቆራጥነትና ፅናት በመታገሉ ነው:: ይህን በመፃረር የሚዋሹት ሁሉ ውጤት አልባ ናቸው:: ኢሕአፓ በትጥቅ ትግል አስፈላጊነት አምኖ ሊሰማራ ሲነሳም ሁኔታው በፈቀደለት ደረጃ ያለውን አጣብቂኝ ሰብሮ ለመውጣት ሲጥር መቸም ቢሆን መቸም ድርጅታዊ ነፃነቱን ሆነ መርሁን አሳልፎ አልሰጠም:: ክህደቱና መሰሎቹ ይህን በተመለከተ የሚዋሹት ያው የጠነዛ ውሸት ከመሆን አላላፈም:: ኢሕአፓ ግን የሚፈልገውን አግኝቶ መርሁን አስከብሮ ትጥቅ ትግሉንም ሊጀምር ችሏል:: ኢሕአፓ የነበረው ርዕዮት ለሕዝብና ለሀገር ይበጃል፤ ትግልን ይቃኛል በሚል የተያዘ እንጂ የሕዝብን ፍላጎትና መብት በመፃረር በሕዝብ ላይ የተጫነም እንዳልነበር ምስክሩ ብዙ ነው:: ኢሕአፓ በሀገራችን ቢቻል ሁሉንም ሀይሎች ያቀፈ ካልሆነም አብዛኛውን ያሰባሰበና ሕዝብ ሊደግፈው የሚችል ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ተቋቁሞ ወድ ዴሞክራሲ እንሸጋጋር አለ እንጂ በማንም ግፊት ሁኔታው የግድ ባላለበት የብረት ትግል ወይም ሞት ብሎ አልተነሳም:: በውስጡም የተነሳውን የአንጃ ችግር በውይይት ሊፈታ መሞከሩም የሚታወቅ ነው:: ወያኔዎቹ መዋሸት እንደጀመሩት ዎች ኢሕአፓ ከወያኔዎች ጋር በአዲስ አባባ ከቶምና መቸም ተገናኝቶ የተወያየ ባይሆንም በአሲምባ ከዘጠኝ ጊዜ ባላነሰ ተገናኝቶ ሰላምና መግባባትን ለማምጣት ሞክሮ አቅቶታል:: ኢሕአ ፓ ከወያኔ ጋር ልዩነቱም እነ ስብሐት ነጋና መሰሎቻቸው ዛሬ እንደሚዋሹት ሳይሆን ወያኔ ትግራይ ካልተገነጠለች ብሎ ወያኔ በመነሳቱና ኢሕአፓንም ከትግራይ ውጣ ብሎ ጦርነት በመክፈቱ ነው::

ሀቅ ታንቃለች አንጂ መነገሯ አይቀርም:: ራሳቸውን ማዋረድ የሚቀናቸው ክፍሎች እንደሚሉት ኢሕአፓ በኤርትራ ግንባሮች የተቋቋመ ሳይሆን በኢትዮጵያ ጀግናና ቆራጥ ልጆች የተመሰረተና በውስጡም የተሰለፉት የኤርትራ ተወላጆች ኤርትራ ብለው ሳይሆን ኢትዮጵያ ብለው ጠባቦችን ታግለው የተሰው መሆናቸውን በ1983 በቋራ ወያኔን ሲታገሉ የተሰዉት እነ ገለብና ጃብር ሳይቀር ምስክር ናቸው:: ኢሕአፓ በምንም ጊዜ የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፎ ለማንም ባዕድ አልቸበቸበም:: ደርግና አልፎም ወያኔ ይህን በመፃረር የለፈፉት ሁሉ ማስረጃ የሌለው ነጭ ውሸት ነው:: ለቻይናም፤ ለሶማሊያም፤ ለአረብም፤ ለሊቢያም ሆነ ለእንግሊዝና አሜሪካ እንደ ሌሎቹ ተጎንብሶ ሀገርን አልሸጠም:: ገዳፊ ሆይ አረብ ነን እኮ፤ የአባቴ ስም ዜናዊ ራሱ የየመን ስም ነው ብለ ዋሽቶ ራሱን አላዋረደም:: ለጥቅማ ጥቅም ሲል በፊርማ ሲሶ የኢትዮጵያን መሬት የሶማሊያ ግዛት ነው ብሎ እንደ ወያኔ  አልሰጠም:: ዛሬም ቢሆን ለሱዳን የኢትዮጵያን መሬት የሰጠና የሀገርን መሬት ለአረቦች፤ቻይናና ህንድ መፈንጫ ያደረገ ኢሕአፓ ነው ወያኔ? ኢሕአፓ ለብሄረሰቦች እኩልነት ታገለ እንጂ ግንጠላ ወይ ሞት በሚል የተሳሳተ ጎዳና አልተጓዘም:: ጠባቦ ችም ትምክህተኞችም ያጠቁትም መርዛቸውን አላስረጭ ስላላቸውና ብሎም ለኢትዮጵያ አንድነ

ትና ለሕዝብ እኩልነት በመቆሙ ነው:: ኢሕአፓ ከሀገር ወዳድ ድርጅቶችጋር አቅማቸው ደካማ በሆነበትም ሁሉ በእኩል ደረጃ በህብረቶች ተሳስሮ ለመታገል ሞክሯል:: ለህብረት ምስረታም ከማንም የበለጠ አስተዋፅዖ ያደረገ ለመሆኑም ምስክር ብዙ ነው:: ዛሬም ራስን በማጠናከሩ ስራ በትኩረት ቢሰማራም በቁርጠኛነት ፀረ ወያኔ ከሆኑና ህልውና ካላቸው ቡድኖች ጋር ለመወያየት ዝግጁነቱን ከገለጠ ውሎ አድሯል እንጂ ፀረ ህብረት ሆኖ አይገኝም/ሆኖም አያውቅም:: ኢሕአፓ መሰረቱ ና ለሁሉም ፖለቲካዊ ውሳኔው መነሻው ያለውን የመለስ አገዛዝ መቃወምና ለመጣል መነሳት የሚል ነውና በዚህም በዚያም ከዚህ ዘረኛና አረመኔ አገዛዝ ጋር መሞዳሞድን የሚሰብኩ ትን ይቃወማል እንጂ አያዳምጥም:: በ1997 ምርጫ ሂደት የህብረት አጋሮቹ መሳተፍን ዘግይተ ውም ቢሆን ሲወስኑ በርካታ ጥያቄዎች ቢኖሩትም ጥረታቸውን ደግፎ እንደነበር ሲታወቅ ከምር ጫው ውጤትና ከፍጅቱ በኋላ ግን ይህንኑ መንገድ በ2002 ዳግም መጓዝ ስህተትና ጎጂም ነው በሚል በምርጫው አትሳተፉ ጥሪን አስደምጧል:: የመለስን አገዛዝ ማቀፍ ሳይሆን በትግል ማር ገፍና መጣል ነው የሚያስፈልገው በሚለው አቅዋም በመፅናቱም ከውስጡ ለወያኔ ማሸርገድን የከጀሉ አንጃዎች ብቅ ብለው ሊያጠቁትና ለወያኔ ተጎንባሽ ሊያደርጉት ሞክረው ቅስማቸውን ሰብሮ የድርጅቱን ህልውናና የጠራ ሕዝባዊ መስመር ጠብቋል:: ኢሕአፓ እንደ ድርጅት በጋራ አመራርና ማዕከላዊነትን በማይሰርዝ ዴሞክራሲ መሰረት የሚሰራ ድርጅት ነውናም ከሁሉም በላይ የሆነ ሊቀመንበር ወይም የሰው ጣዖት ሰይሞና አቁሞ አያውቅም:: ሕዝብ ነው ለሁሉም በላይ የሚለውም አቅዋሙ ከዚሁ ፀረ ጣዖት እምነቱ ጋር ተያይዞ ሲከሰት አምልኩን ባዮችና ጭፍሮቻቸው እንዳልወደዱለት ደግሞ የሚታወቅ ነው::

ኢሕአፓ ትላንትም ዛሬም በህቡዕ የሚታገል ድርጅት ነው--ወዶ ሳይሆን ሁኔታው የግድ ያደረገ ው በመሆኑም ነው:: ስለዚህም ግልጥልጥ ዝርክርክ ብሎ ራሱንም ሕዝብንም ለጠላት ጥቃት አሳልፎ መስጠት አይጠበቅበትም/አያደርገውምም:: አፈና ባልሰፈነበት ቦታዎች ያሉ ዜጋዎች የህገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ በመዘንጋት የኢሕአፓን ህቡዓዊነት በአሉታዊ ሊገመግሙ መነሳታ ቸው ተደጋግሞ የታየ ቢሆንም ህቡዓዊነቱ ልዩ ምስጢር ያለው ሳይሆን ራስን ከጥቃት ለመከላከ ል መሆኑ መታወቅ ያለበትም ነው:: ህቡዓዊነት ለነበርን ዋሾዎች ቢያመችም ለድርጅቱ ቀጣይ ህልውና በጣም ወሳኝነት ያለው መሆኑ የሚዘነጋ ሊሆን አይችልም:: ዋሾዎች ኢሕአፓን በውሸት እያጠቁ ድርጅቱን ለማያውቁት የተሳሳተ ግንዛቤን፣ ፍርሃትና ጥርጣሬንም ቢሰጡም ድርጀቱ ለሕዝብ ብሎ የቆመ ኢትዮጵያዊ ድርጅት እንደነበርም እንደሆነም ማንም ሊክደው የሚችል አይደለም:: አዲሱ ትውልድም ይህንን መገንዘብ ይኖርበታል:: መሰዋዕትነትን የማይጠይቅ ትግል ምስጢሩ ቢያንስ ለኢሕአፓ ግልፅ ሊሆን አልቻለምና ( ቀንበርን ዝም ብሎ ከመቀበል ባሻገር!) ደርግንም ሲታገል " አልቋል" ከወያኔም ሲታገል እንዲሁ ከባድ መስዋዕትነትን ከፍሏል፣ ለመክፈልም ተዘጋጅቶ ትግሉን አፋፍሟል:: ነፃነትና መብት ከተፈለገ ፀረ ሕዝብ አገዛዝን ቆርጦ ከመታገልና መስዋዕትነትንም በድፍረት ከመቀበል ሌላ አማራጭ የለም:: የሚለፈፈው የሰላማዊ ትግል አማራጭ አውን ሊሆን የማይችል-- ቡና የለም እንጂ ውሃማ ቢኖር ዓይነት--

የምትህት አማራጭ ነውናም ኢሕአፓ ሕዝብን ባልሆነ መንገድ ቃኝቶ ሊያታልል ወይም ለነመለ ስ ሰለባ ሊያደርግ ምንም ፍላጎት የለውም፡፡ ኢሕአፓ ካለፈውም ካለውም አገዛዝ ተጠቃሚ ካለመሆኑ ሌላ መርህና ሕዝብን ሽጦም ተጠቃሚና ፍርፋሪ ለቃሚ ሊሆን አይፈልግም፡፡ ለዚህም ነው በፀረ ወያኔው ትግል ሰፊውን ሕዝብ ለማሰለፍ በሚያደርገው ጥረት ላይ ደንቃራ ሊሆን የሚፈልገውን የመለስ ቡድንና ቅጥረኞቹን የውሸት ዘመቻ በማጋለጥ ላይ ያለው፡፡ በተለይ አዲስ ትውልድ በዋሾዎቹ ተደናግሮ ከኢሕአፓ ጎን መሰለፍን ወይም ለኢትዮጵያ መታገልን እንዳይተ ው፡፡ ለትግል እንዲነሳሳ፡፡ ሕዝባዊ ትግል መሰረቱ ሀቀና ሀቀኝነት ነውና የውሸትን ግንብ ማፍረስ ና የውሸት ምስጦችንም መበታተን ይገባናል፡፡

ዝም ከተባለ ሐሰተኛ ምስክር ጉልበት ይሰብራል፡፡ ውሸት ሲበዛም እውነት ዋዛ ይሆናል፡፡ ለዚህም ነው ጠባቦች  የኢትዮጵያን ታሪክ የሚበርዙትና የሚክዱት፡፡ ኢሕአፓም ሐሰተኛ ብርቱ ወንጀለ ኛ ብሎ እነሆ ለምን ይዋሻል እስከመቼስ ይዋሻል በሚል የሐሰተኞችን ጎራ ሀቁን በመዘርዘር ያጋ ልጣል፡፡

ድል ለሀቅ ወዳጹ የሀገራችን ሰፊ ሕዝብ!
እናቸንፋለን!!